# መስቀል ተመርኩዞን

መስቀል ተመርኩዞን ወንጌል ተጫምተን

ሃይማኖትን ሰብከን በክርስቶስ አምነን

ማን ያሸንፈናል እኛ ክርስቲያን

ክርስቶስ አለለን

ንግሥትቷ ዕሌኒ በጣም የታደለች

በዕጣን ጢስ ተመርታ መስቀሉን አገኘች

መድኃኒት ስትፈልግ ኪራኮስን ይዛ

መስቀሉን አገኘች የዓለሙን ቤዛ።

መስቀል ተመርኲዘን ወንጌል ተጫምተን
ሃይማኖትን ሰብከን በክርስቶስ አምነን
ማን ያሸንፈናል እኛ ክርስቲያን
ክርስቶስ አለለን

ሙታንም ተነስተው ያመሰገኑት
ዕፀ መስቀሉ ነው የእኛ መድኃኒት
መስቀል ምርኲዛችን ጎዳናው ወንጌል
ወደ ገነት እንጂ አንሄድም ሲዖል።

መስቀል ተመርኲዘን ወንጌል ተጫምተን
ሃይማኖትን ሰብከን በክርስቶስ አምነን
ማን ያሸንፈናል እኛ ክርስቲያን
ክርስቶስ አለለን

ንዑ ንወድሶ ለእፀ መስቀል
የተሸከመውን የአምላክን ቃል
ንዑ ንወድሳ ለማርያም ድንግል
አክሊለ ምዕመናን ምክሃ ደናግል።

✝✝✝ ✝✝✝ ✝✝✝

# ደስ ይበለን

ደስ ይበለን እልል በሉ (፪)

አልቀረም ተቀብሮ ተገኘ መስቀሉ (፪)

በብርሃን መላት ዓለምን በሙሉ (፪)

ምን ቢተባበሩ ምቀኞች ቢጥሩ (፪)

ቅዱስ መስቀሉንም ሸሽገው ቢሰወሩ (፪)

አልቻሉም ሊያጠፉት ምን ቢተባበሩ (፪)

ደስ ይበለን እልል በሉ (፪)
አልቀረም ተቀብሮ ተገኘ መስቀሉ (፪)
በብርሃን መላት ዓለምን በሙሉ (፪)
በተራራ ተሰውሮ ለዘመናት (፪)
ተጥሎ በተንኮል ተደብቆ ከኖረበት (፪)
ተገለጠ ዛሬ በደመራ እሳት (፪)

ደስ ይበለን እልል በሉ (፪)

አልቀረም ተቀብሮ ተገኘ መስቀሉ (፪)

በብርሃን መላት ዓለምን በሙሉ (፪)

ዕሌኒ ናት ይህን ምስጢር ያስገኘችው (፪)

ደመራን በቦታው በጥበብ ያስቆመችው (፪)

የተንኮልን ተራራ ያስቆፈረችው

ደስ ይበለን እልል በሉ (፪)

አልቀረም ተቀብሮ <u>ተገኘ መስቀሉ</u> (፪)

በብርሃን መላት ዓለምን በሙሉ (፪)

ታሪካዊ የክርስቶስ <u>ሕያው መስቀል</u> (፪)

ተገለጠ ዛሬ በክብር <u>በግሩም ኃይል</u> (፪)

ምንጊዜም ሲያበራ እንዲህ ይኖራል (፪)

# ኀበ ቀራንዮ

ኀበ ቀራንዮ ደብረ መድኃኒት (፬)
ቀራንዮ (፪) ኀበ ቀራንዮ (፪)
የመስቀሉ ቃል ለእኛ የእግዚአብሔር ኃይል ነው (፬)
ለማያምኑት ሞኝነት ነው ለእኛ ግን ሕይወት ነው (፪)
እንመሰክራለን ፈጣሪያችን አለ(፬)
እንመነው አንካደው ፈጣሪያችን ቸር ነው (፪)
እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት (፬)
እንመናት አንካዳት የአምላክ እናት ናት (፪)
ኀበ ጥበባት ኀበ ልሳናት(፬)
ዮሐንስ (፪) ወንጌለ ሰብከት (፪)

✝✝✝ ✝✝✝ ✝✝✝